ቁጥር - ሕ1162/11/546
ታሕሣስ 2 9 2016

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ፖሊስ

ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ሠላምና ፀጥታ

ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ርዕሰ መስተዳደር

<u>ሆሳዕና</u>

ጎጎት ለጉራጌ አንድነት እና ፍትሕ ፓርቲ በቀን 26/04/2016ዓ.ም በቁጥር ጎፓ/007/2016 በተፃፈ ደብዳቤ የፓርቲያቸው ከፍተኛ አመራር አቶ መላኩ ይራዳው፣ አቶ ጌዲዮን በጋለ እና ሃይደር ሙራድ አዲስ አበባ ከሚገኘው መኖርያ ቤታቸው በፖሊስ ተይዘው በአሁኑ ሰዓት ሆሳዕና ከተማ በሚገኘው ሐዲያ ዞን ፖሊስ መምርያ ታስረው የሚገኙ መሆኑን፤ አቶ ጀምበር አብዶ ደግሞ ታህሣሥ 25 ቀን 2016 ዓ.ም ቡታጅራ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከዚህ ቀደም በተከሰሱበት ክስ በዋስ ከተለቀቁ በኋላ ችሎት ለመከታተል በተገኙበት በፖሊስ ተይዘው ቡታጅራ ከተማ ፖሊስ መምሪያ መሆናቸውን እና ከወልቂጤ ከተማ የተያዙት ሌላኛው አመራር አቶ ትዕግስቱ ንጋቱ ደግሞ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ልዩ ኃይል ካምፕ ውስጥ ታስረው እንደሚገኙ ገልፀዋል። አቶ መስፍን አበራ በደረሰባቸው ከፍተኛ ድብደባ ምክንያት የቀዶ ጥገና ህክምና ተደርጎላቸው ህክምና እየተከታተሉ መሆኑን ገልፀው ሌሎች አመራሮቻቸው እና አባሎቻቸው ላይ ወከባ እና ማስፈራሪያ እየተፈፀመባቸው መሆኑን በመግለፅ ለቦርዱ አቤቱታ አቅርበዋል።

በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 መሰረት የፖለቲካ ፓርቲዎችን ማስተዳደር፣ በአመራርና በአባላቱ ላይ የሚደርስ ማናቸውንም ጉዳይ መከታተል ቦርዱ ከተጣሉበት ኃላፊነቶች መካከል አንዱ ነው።



ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለ ከተማ
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ - ገጽ
www.nebe.org.et

በመሆኑም ፓርቲው ከላይ ያቀረበውን ቅሬታ በማጣራት እስከ ጥር 04 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ማብራሪያ እንዲሰጥ ቦርዱ ያሳውቃል።

ከአክብሮት ሠላምታ ጋር

ሜላትወርቅ ኃይሉ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ
ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ

ግልባጭ፤

- ጎኅት ለጉራጌ አንድነት እና ፍትሕ ፓርቲ